# የመዋለ ሕጻናት አማራጮች - ማዕከላት እና ቤቶች

**የመዋለ ሕጻናት ማዕከላትና የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ቤቶች ጥቅማቸውና ጉዳታቸው**

**የመዋለ ሕጻናት ማዕከላት**
በምድብ የሙሉ ወይም የግማሽ ቀን መዋለ ሕጻናት አገልግሎት። ልጆች ከዕድሜ እኩያቸው ጋር ይመደባሉ። ማዕከላቱ ቁሳቁሶችንና ለዕድሜ ተገቢ የሆኑ የታቀዱ ተግባራትን ያቀርባሉ። ትናንሽ ማዕከላት በቀኑ ከፊል ጊዜ ውስጥ በዕድሜ የተለያዩ ልጆች የተቀላቀሉበት ምድብ ሊኖሯቸው ይችላሉ።

### ጥቅማቸው

- የሚያስመካ/አስተማማኝ፡ ዓመቱን ሙሉ ለሥራ ክፍት ነው፡ የአገልግሎቱ መኖር በአስተማሪ መታመም ወይም ዕረፍት ላይ መሆን አይጋደልም።
- ከወላጆች ጋር አብሮ የመወያየና ለመገናኛ ዕቀድ።
- ልጆች ከዕድሜ እኩያቸው ጋር ለመዋል የሚያስችላቸው ዕድል።

### ጉዳቶቹ

- የሥራ ሰዓታቸው ዘግይቶ የሆነ፡ ቀደም ያለ ለሆነ፡ የሚለዋወጥ ወይም የግማሽ ቀን የሥራ ጊዜ ያላቸውን ወላጆች ፍላጎት ላያሟላ ይችላል። ብዙውን ጊዜ በወላጆች የሥራ ጊዜዎች ወይም ድንገተኛ ጊዜዎች ለውጦች ላይ በቀላሉ ለማመቻቸት ያስቸግራል።

- በዛ ያሉ ልጆች ያሉባቸው ምድቦችና የሥራ ባልደረቦች ቋሚ ያለመሆን ሁኔታ ለአንዳንድ ልጆችና ወላጆች ችግር ሊፈጥር ይችላል።

- በሙሉ ቀን ማዕከል ውስጥ ለግማሽ ቀን ብቻ ወይም ከአንድ ሙሉ ሳምንት ያነሰ ጊዜ የሚቀዩ ልጆች ጓደኝነትን ለመመስረተ ወይም ሙሉ ቀን ከሚቀዩት አብዛኞቹ ልጆች ለመላመድ በጣም ሊያስቸግራቸው ይችላል፡ የተረጋጋ ሁኔታ ላይሰማቸው ይችላል።

### ለመዋለ ሕጻናት የሥራ ፈቃድ አስፈላጊ ነጥቦች
### ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ ፕሮግራም የሥራ ፈቃድ አስፈላጊ ነጥቦች።

የመዋለ ሕጻናት ማዕከል የሠራተኛ-ልጅ ቁጥር ሲመዛዘን

| የልጆቹ ዕድሜ | የሠራተኛ ከልጅ ቁጥር ጋር ሲመዛዘን | ከፍተኛው የምድብ ብዛት |
|---|---|---|
| ከ 1 ወር እስከ 11 ወር | 1:4 | 8 |
| 12 ወር እስከ 29 ወር | 1:7 | 14 |
| 30 ወር እስከ 5 ዓመት | 1:10 | 20 |
| 5 ዓመትና በላይ | 1:15 | 30 |

**የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ቤቶች**
በግለሰብ ቤት የሙሉ ወይም የግማሽ ቀን መዋለ ሕጻናት አገልግሎት። የመኖሪያ ቤት ዓይነት ዝግጅት ያለው ዕድሜያቸው የተለያዩ የሆኑ ልጆች ያሉበት ምድብ።

### ጥቅሞቹ

- አንዳንድ ልጆች የሚፈልጉት አነስተኛ ቁጥር ያለው ምድብ

- በሚቀዩበት ቀን ልጆች ከጥቂት አዋቂ ሰዎች ጋር መዋል መቻል አለባቸው እናም ከጠባቂያቸው ጋር የጠበቀ መቀራረብ ለመፍጠር ዕድል ይሰጣቸዋል።

- ሰዓትን፡ የግማሽ ቀን ሥራን ወይም መደበኛ ያልሆነ የሥራ ጊዜን በተመለከተ ከመዋለ ሕጻናት ማዕከል በተሻለ የአገልግሎቱ ሁኔታ እንደሚያመች መሆን የሚችል።

- ብዙውን ጊዜ በማህበረተሰብ ውስጥ የሚገኙ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ዓይነቶች፡ ሰፋ ያለ የተለያየ ዓይነት የእንክብካቤ ዝግጅቶች ሊገኙ ይችላሉ።

- የመኖሪያ ቤት የመሰለ ዝግጅት፡ የአንዳንድ ልጆችን ፍላጎት በተሻለ ሊያሟላ ይችላል።

- ክፍያው ከመዋለ ሕጻናት ማዕከል ወይም ከመኖሪያ ቤት ውስጥ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ትንሽ አነስ ሊል ይችላል።

- ጉዳቶቹ፡

  - አገልግሎት አቅራቢው በሚታመሙ ጊዜ ወይም እረፍት በሚሄዱ ጊዜ መጠባበቂያ የልጅ መዋያ ያስፈልጋል።

  - አስተማማኝነቱ በአገልግሎት አቅራቢው ጤንነት ወይም የግል ሁኔታዎች መለዋወጥ የተወሰነ ሊሆን ይችላል።

  - ወላጆችና አገልግሎት አቅራቢዎች ጥብቅ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን በሁለቱ መካከል ግንኙነቱ ጥሩ ካልሆነና ልጅ የማሳደጉ ዘዴ በጣም የሚለያይ ከሆነ ቀሬቴ ሊያመጣ ይችላል።

- ለቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ቤቶች የሥራ ፈቃድ አስፈላጊ ነጥቦች

የቤሰብ መዋለ ሕጻናት የአቂዎችና የልጆች ቁጥር ሲመዛዘኑ፡

| ቁጥር ወይም የሚያስፈልገው አገልግሎት አቅራቢ | የዕድሜ ክልል በዓመት | ከሁለት ዓመት በታች ከፍተኛው የልጆች ቁጥር | ከፍተኛው የልጆች ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ባለፈቃዱ | ከልደት - 11 | 2 | 6 |
| የአንድ ዓመት ልምድ ያለው ባለፈቃድ | 2-11 | ምንም | 8 |
| የአንድ ዓመት ልምድ ያለው ባለፈቃድ | 5-11 | ምንም | 10 |
| የአንድ ዓመት ልምድ ያለውና ረዳት ያለው ባለፈቃድ | ከልደት - 11 | 4 | 9 |
| የሁለት ዓመት ልምድና የስልጠና ትምህርት ያለው ባለፈቃድ | 3-11 | ምንም | 10 |
| የሁለት ዓመት ልምድ የስልጠና ትምህርትና ረዳት ያለው ባለፈቃድ | ከልደት - 11 | 4 | 12 |

**ረጂ ጽሑፍ**

- የመጠባበቂያ መዋለ ሕጻናት አገልግሎት መረጃና ጥቆማ ዛሳብ
- ቤተሰቦች ሁሉ አንድ ዓይነት አይደሉም

**በተጨማሪም ይመልከቱ**

- ቅድመ ትምህርት ቤት መዋለ ሕጻናት
- ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ መዋለ ሕጻናት
- ኤዩ ፔርስ (ረዳት)
- ሞግዚት
- ቤተሰብ፡ ጓደኞችና ጎረቤቶች